ብጹእ አቡነ ቴዎፍሎስ ዶ/ር የሰሜን ካሊፎርኒያ ኔቫዳ እና አሪዞና ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ እና ብጹእ አቡነ ጴጥሮስ ዶ/ር የኒውዮርክ እና አካባቢው ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ በአዲስ መልክ በኢትየኦጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የሥነ ሕንጻ ዲዛይን ለሚገነባው የላስ ቬጋስ ደብረ ምሕረት ቅ/ሚካኤል ቤ/ክርስቲያን የመሠረት ድንጋይ አኖሩ። የላስ ቬጋስ ደብረ ምሕረት ቅ/ሚካኤል ቤ/ክርስቲያን በከተማው የመጀመሪያው የኢት/ኦ/ተ/ቤ/ክርስቲያን ሲኾን በቀድሞው የሀገረ ስብከት መዋቅር (ከ ፲፱፻፺፱ - ፳፻፬ ዓ/ም) የ ብጹእ አቡነ ዮሴፍ ሊቀ ጳጳስ ሀገረ ስብከት መንበረ ጵጵስና እንደነበር ይታወቃል።

በተጨማሪም ታቦተ ቅዱስ ሚካኤል ወደ ላስ ቬጋስ ከተማ መጥቶ መንፈሣዊ አገልግሎት በከተማው የተጀመረው እ.ኤ.አ ከ 2004 ዓ/ም ጀምሮ ሲኾን በደብሩ አሁን አገልገሎት የሚሰጥበት ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን በቀድሞው የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ብጹእ አቡነ ዮሴፍ እና በብጹአን አበው ሊቃነ ጳጳሳት ሐምሌ ፭ ቀን ፳፻፮ ወይም July 12, 2014 ተባርኮ መንፈሣዊ አገልግሎት መስጠት የጀመረ አንጋፋ ደብር ነው። ስለሆነም በአሁን ጊዜ በከተማው የምዕመናን ቁጥር መጨመር ምክንያት እና ደብሩን ወደ ተሻለ የሥነ ሕንጻ ዲዛይን እና ስፋት ለማሳደግ በተቀረጸ የረዥም ጊዜ እቅድ የደብሩ ሰበካ ጉባዔ አስተዳደር ተጨማሪ 3 ኤከር ባዶ መሬት በመግዛት አዲሱ ሕንጻ ቤ/ክርስቲያን ለሚሠራበት ቦታ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ብጹእ አቡነ ቴዎፍሎስ ዶ/ር እና ብጹእ አቡነ ጴጥሮስ ዶ/ር የኒውዮርክ እና አካባቢው ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ ሰኔ ፲፩ ቀን ፳፻፲፫ ( June 18,2016) ቡራኬ በማድረግ የመሠረት ድንጋይ አኑረዋል። በዋዜማው መርሐግብር በላስ ቬጋስ የሚገኙ የሦሥቱም አጥቢያ ማህበረ ካህናት ፣ ተጋባዥ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ካህናት ፣ ዘማርያን ፣ ምዕመናን እና ከተለያየ የስቴት ከተሞች የመጡ ዲያቆናት በዋዜማ በዓሉ ተሳታፊ በመኾን የዋዜማው ሥርዓት በታላቅ ድምቀት ተከናውኗል።

በመጨረሻም ደብሩን ለረዥም ዓመታት ከሎስ አንጀለስ ከተማ በመመላለስ በቀድሞው የምንኩስና ማዕረጋቸው ያገለገሉት የአሁኑ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ብጹዕ አቡነ ቴዎፍሎስ ዶ/ር ከ 2011 ዓ/ም ጀምሮ ደብሩ በመንበረ ስብከታቸው ሥር በመኾኑ በክብረ በዓላት በመገኘት ቡራኬ በመስጠት እና አባታዊ ምክር እና የማጽናናት ኃላፊነታቸውን እየተወጡ በመኾኑ እና በዚህ የደብሩ ታሪካዊ ዕለት የመሠረት ድንጋይ ባርከው ማኖራቸው ዕለቱን የበለጠ ታሪካዊ ስለሚያደርገው ለብጹዕነታቸው እና በላስ ቬጋስ ከተማ የደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ለኾኑት የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ መልአከ ስብሃት ቆሞስ አባ ኃይለ ኢየሱስ ገሰሰ የሀገረ ስብከቱ አስተዳደር ጉባዔ የእንኳን ደስ አለዎት መልዕክት አስተላልፏል።